# ትምህርት 36

1. ሙሴ በሲና ተራራ ላይ ከእግዚአብሔር ጋር በመነጋገር ላይ ሳለ እስራኤላውያን ከተራራው ግርጌ ምን ያደርጉ ነበር?

ሀ- እስራኤላውያን ከወርቅ ጥጃ ሠርተው ያመለኩ ነበር።

2. እስራኤላውያን የወርቅ ጥጃ እያመለኩ እንደ ነበር እግዚአብሔር አውቋል?

ሀ- አዎን።

3. እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ ተቆጥቶ ነበር?

ሀ- አዎን።

ለ- እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ እጅግ ስለ ተቆጣ ሊያጠፋቸው ፈለገ።

4. እግዚአብሔር እስራኤላውያንን በሙሉ ያላጠፋቸው ለምን ነበር?

ሀ- ምክንያቱም ሙሴ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን እንዳያጠፋቸው ስለጸለየ ነው።

5. ሙሴ ከሲና ተራራ ግርጌ እንደደረሰ ምን አደረገ?

ሀ- ሙሴ በእስራኤላውያን ላይ በጣም ስለ ተናደደ የእግዚአብሔር ትእዛዛት የተጻፈባቸውን ሁለቱን የምስክር ጽላቶች ወርውሮ ሰባበራቸው።

6. ሙሴ ከእግዚአብሔር የተቀበለውን ሁለት የምስክር ጽላቶች ስለ ሰባበራቸው እግዚአብሔር ሙሴን ምን አድርግ አለው?

ሀ- እግዚአብሔር፥ ሙሴ ሌሎች ሁለት የድንጋይ ጽላቶች ጠርቦ እግዚአብሔር በድጋሚ አሥርቱን ትእዛዛት እንዲጽፍባቸው ወደ ተራራው

ጫፍ እንዲያመጣቸው ነገረው።

7. እስራኤላውያን ልክ እግዚአብሔር ባዘዛቸው መሠረት የማደሪያውን ድንኳን ባይሠሩ ኖሮ የእግዚአብሔር ክብር በድንኳኑ ውስጥ ይገባ ነበር?

ሀ- አይገባም።

8. እስራኤላውያን በራሳቸው መንገድ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ችለዋል?

ሀ- አልቻሉም።

9. እስራኤላውያን ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ የሚችሉበት ብቸኛው መንገድ ምን ነበር?

ሀ- የእግዚአብሔር መንገድ።

10. የእግዚአብሔን መንገድ እንዴት ማወቅ እንችላለን?

ሀ- በእግዚአብሔር መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ አማካኝነት።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ከግብፅ ከባርነት ያወጣና ይመራ ዘንድ ሙሴን መረጠው?

- ሙሴ የእግዚአብሔር መልእክተኛም ነበር።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን መናገር ሲፈልግ ለእስራኤላውያን ይነግር ዘንድ ለሙሴ ይናገር ነበር።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን መናገር የፈለገውን ሁሉ እንዲናገር ሙሴን መራው።

- በተጨማሪም እግዚአብሔር በጽሑፍ እንዲተላለፍ የፈለጋቸውን ነገሮች ሁሉ እንዲጽፍ እግዚአብሔር ሙሴን መራው።

- በእግዚአብሔር መጽሐፍ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን የመ ጀመሪያዎቹን አምስት መጻሕፍት የጻፈው ማን ነበር?

- ሙሴ ነበር።

- ሙሴ ምን መጻፍ እንዳለበት እንዴት አወቀ?

- እግዚአብሔር የፈለገውን ሁሉ እንዲጽፍ ሙሴን ስለመራው።

- እስራኤላውያን ግብፅን ለቅቀው በምድረ በዳ ውስጥ ይጓዙ ነበር።

- እስራኤላውያን በምድረ በዳ በመጓዝ ላይ ሳሉ፥ የሚሄዱበትን መንገድ በምን አወቁ?

- እግዚአብሔር መራቸው።

ዘጸአት 40፡36-38

36- በእስራኤላውያን ጉዞ ሁሉ ደመናው ከማደሪያው ላይ በተነሣ ጊዜ፣ ይጓዙ ነበር፤

37- ደመናው ካልተነሣ ግን፣ እስሚነሣበት ቀን ድረስ አይጓዙም ነበር።

38- ስለዚህ በጉዞአቸው ወቅት፣ በእስራኤል ቤት ፊት ሁሉ የእግዚአብሔር ደመና በቀን ከማደሪያው በላይ፣ በሌሊትም እሳቱ በደመናው ውስጥ ነበር።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን እንዲቆሙ ሲፈልግ ደመናው ባለበት እንዲቆም ያደርገው ነበር።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያን እንዲጓዙ ሲፈልግ ደመናው እንዲሄድ ያደርገው ነበር።

- አሥርቱን ትእዛዛት ለእስራኤላውያን ከሰጠ በኋላ እና እስራኤላውያንም የማደሪያውን ድንኳን ከሠሩት በኋላ እግዚአብሔር ደመናውን አነሣው።

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የመራቸው ወዴት ነበር?

- እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የመራቸው ለቅድመ - አባታቸው ለአብርሃም ተስፋ ወደ ገባለት ወደ ከነዓን ምድር ነበር።

- እስራኤላውያን ደመናውን እየተከተሉ እግዚአብሔር ወደ ከነዓን ድንበር መራቸው።

- እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ድንበር እንደ ደረሱ እግዚአብሔር ሙሴን ምን እንዲያደርግ ነገረው?

ዘኍልቍ 13፥1-2

1- እግዚአብሔር ሙሴን እንዲህ አለው፤

2- «ለእስራኤላውያን የምሰጣቸውን የከነዓንን ምድር እንዲሰልሉ ጥቂት ሰዎች ላክ፤ ከእያንዳንዱም የአባቶች ነገድ አለቃ ይላክ።»

- እግዚአብሔር ሙሴን ከአሥራ ሁለቱ ነገድ ምድሪቱን የሚሰልሉ አንድ አንድ ሰው እንዲመርጥ ነገረው።

- ሙሴ እግዚአብሔርን በመታዘዝ አሥራ ሁለቱ ሰዎች ምድሪቱን እንዲሰልሉ ላከ።

ዘኍልቁ 13፡3

3- ስለዚህ ሙሴ በእግዚአብሔር ትእዛዝ ከፋራን ምድረ በዳ እነዚህን ላካቸው፤ ሁሉም የእስራኤላውያን አለቆች ነበሩ።

- ሙሴ የከነዓንን ምድር እንዲሰልሉ አሥራ ሁለቱን ሰዎች ከመላኩ በፊት ምን አላቸው?

ዘኍልቁ 13፡17-21

17- ሙሴም ከነዓንን እንዲሰልሉ በላካቸው ጊዜ እንዲህ አላቸው፤ «ኔጌብን ዘልቃችሁ ወደ ተራራማው አገር ግቡ።

18- ምድሪቱም ምን እንደምትመስልና የሚኖሩበትም ሰዎች ብርቱዎች ወይም ደካሞች፣ ጥቂቶች ወይም ብዙዎች መሆናቸውን እዩ።

19- የሚኖሩበት ምድር ምን ዓይነት ናት? መልካም ወይስ መጥፎ? የሚኖሩባቸውስ ከተሞች ምን ይመስላሉ? በግንብ ያልታጠሩ ናቸው ወይስ የተመሸጉ?

20- ዐፈሩስ እንዴት ያለ ነው? ለም ወይስ ደረቅ? ደናም ወይስ ደን አልባ? በተቻለ መጠን ከምድሪቱ ፍሬ ይዛችሁ ኑ።»

21- ስለዚህ ወጥተው ከጺን ምድረ በዳ አንሥቶ በሴቦ ሐማት በኩል እስከ ረአብ ድረስ ዘልቀው ምድሪቱን አጠኑ።

- ከአርባ ቀናት በኋላ አሥራ ሁለቱ ሰዎች የከነዓንን ምድር ሰልለው ተመለሱ።

- አሥራ ሁለቱ ሰዎች ስለ ከነዓን ምድር ለሙሴና ለእስራኤላውያን የነገሯቸው ይህ ነው።

ዘኍልቁ 13፡27-29

27- ለሙሴም እንዲህ ብለው ነገሩት፤ «ወደ ላክኸን ምድር ዘልቀን ገባን፤ ማርና ወተት የምታፈስስ ናት፤ ፍሬዋም ይኸው።

28- በዚያ የሚኖሩት ሰዎች ግን ኃያላን ሲሆኑ፣ ከተሞቹም የተመሸጉና ትላልቅ ናቸው፤ እንዲያውም የዔናቅን ዝርያዎች በዚያ አይተናል።

29- አማሌቃውያን የሚኖሩት በኔጌብ፣ ኬጢያውያን፣ ኢያቡሳውያንና አሞራውያን በኰረብታማው አገር፣ ከነዓናውያን የሚኖሩት ደግሞ በባሕሩ አቅራቢያና በዮርዳኖስ ዳርቻ ነው።»

- የከነዓን ምድር ማርና ወተት የሚታፈስ አገር ናት።

- እንዲሁም ደግሞ ግዙፍና ኃያላን ሰዎችም ያሉባት አገር ናት።

- የከነዓን ከተሞች ጠንካራና ከፍታ ባላቸው ቅጥሮች የተከበቡ ነበሩ።

- ከነዓንን ሊሰልሉ ወደ ከነዓን ከሄዱት አሥራ ሁለት ሰዎች አሥሩ በእግዚአብሔር አልታመኑም።

- በእግዚአብሔር ያልታመኑት አሥር ሰዎች ለእስራኤላውያን ምን አሏቸው?

ዘኍልቁ 13፡31-33

31- ከእነርሱ ጋር የወጡት ሰዎች ግን፣ «ከእኛ ይልቅ ብርቱዎች ስለሆኑ፣ ልናሸንፋቸው አንችልም» አሉ።

32- እነዚህም ስለ ሰለሏት ምድር በእስራኤላውያን መካከል እንዲህ የሚል መጥፎ ወሬ አሰራጩ፤ «ያየናት ምድር የሚኖሩባትን ሰዎች የምትበላ ናት፤ እዚያ ያየናቸው ሰዎች ሁሉ ግዙፎች ናቸው፤

33- ኔፊሊምንም በዚህ አይተናል። የዔናቅ ዝርያዎች የመጡት ከኔፊሊም ነው። ራሳችንን ስናየው እንደ አንበጣ ነበርን፤ በእነርሱ ዓይን የታየነውም በዚሁ መልክ ነበር።»

- በእግዚአብሔር ያልታመኑት አሥሩ ሰዎች ወደ ከነዓን መግባት ያልፈለጉት ለምን ነበር?

- አሥሩ ሰዎች በከነዓን የሚኖሩትን ግዙፍና ኃያላን ሰዎች ፈርተው ስለ ነበር ነው።

- አሥሩ ሰዎች እግዚአብሔር የከነዓንን ሰዎች የማሸነፍ ኃይል እንዳለው ስላላመኑ ነው።

- አሥሩ ሰዎች እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የከነዓንን ምድር ሊሰጥ የገባውን ቃል ስላላመኑ ነው።

- አሥሩ ሰዎች እስራኤላውያን ወደ ከነዓን መግባት እንደሌለባቸው ነገሯቸው።

- ከአሥራ ሁለቱ ሰላዮች መካከል በእግዚአብሔር ያመኑ ሁለት ሰዎች ነበሩ።

- ስማቸውም ካሌብና ኢያሱ ይባላል።

- ካሌብና ኢያሱ እስራኤላውያንን ምን አሏቸው?

ዘኁልቁ 13፡30

30- ከዚያም ካሌብ ሕዝቡን በሙሴ ፊት ጸጥ አሰኝቶ፣ «እንውጣ! ምድራቸውን እንውረስ፤ ማሸነፍም እንችላለን አላቸው።»

- ካሌብና ኢያሱ ወደ ከነዓን ምድር መግባት የፈለጉት ለምን ነበር?

- ካሌብና ኢያሱ በከነዓን የሚኖሩት ግዙፍና ኃያላን ሰዎችን ስላልፈሩ።

- ካሌብና ኢያሱ እግዚአብሔር የከነዓንን ሰዎች የማሸነፍ ኃይል እንዳለው ስላመኑ።

- ካሌብና ኢያሱ እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን የገባውን ቃል እንደሚፈጽመውና የከነዓንን ምድር እንደሚሰጥ ስላመኑ።

- ካሌብና ኢያሱ እስራኤላውያን እግዚአብሔርን በመታዘዝ ወደ ከነዓን መግባት እንዳለባቸው አመኑ።

- እስራኤላውያን የሰሙት በእግዚአብሔር ያልታመኑትን አሥር ሰዎች ወይስ በእግዚአብሔር ያመኑትን ካሌብንና ኢያሱን ነበር?

ዘኁልቁ 14፡1-4

1- በዚያች ሌሊት ማኅበረሰቡ ሁሉ ድምፁን ከፍ አድርጎ ጮኸና አለቀሰ።

2- እስራኤላውያን በሙሉ በሙሴና በአሮን ላይ አጉረመረሙ፤ ማኅበሩም ሁሉ እንዲህ አላቸው፤ «ምነው በግብፅ ወይም በዚህ ምድረ በዳ

ሞተን ባረፍነው ኖሮ፤

3- እግዚአብሔር ወደዚች ምድር የሚያመጣን ለምንድን ነው? በሰይፍ እንድንወድቅ ነውን? ሚስቶቻችንና ልጆቻችንም ይማረካሉ፤ ታዲያ ወደ ግብፅ መመለሱ አይሻለንም?»

4- እርስ በርሳቸውም፣ «አለቃ መርጠን ወደ ግብፅ እንመለስ» ተባባሉ።

- እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ያልታመኑትን አሥር ሰዎች በመስማት ወደ ከነዓን ምድር ለመግባት እምቢ አሉ።

- ካሌብና ኢያሱ በድጋሚ ለእስራኤላውያን ተናገሯቸው።

ዘኁልቁ 14፡6-9

6- ምድሪቱን ከሰለሏት መካከል የነበሩት የነዌ ልጅ ኢያሱና የዩፎኒ ልጅ ካሌብ ልብሳቸውን ቀደዱ፤ ለመላው የእስራኤል ማኅበርም እንዲህ አሉ።

7- «ዞረን ያየናትና የሰለልናት ምድር እጅግ ሲበዛ መልካም ናት።

8- እግዚአብሔር በእኛ ደስ ከተሰኘብን ማርና ወተት ወደምታፈሰው ወደዚያች ምድር መርቶ ያገባናል፤ ለእኛም ይሰጠናል።

9- ብቻ በእግዚአብሔር ላይ አታምፁ፤ እንደ እንጀራ እንጎርሳቸዋለንና የምድሪቱን ሰዎች አትፍሯቸው። ጥላቸው ተገፎአል፤ እግዚአብሔርም ከእኛ ጋር ነውና አትፍሯቸው።»

- ካሌብና ኢያሱ እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ላይ እንዳያምፁ ለመኗቸው።

- ካሌብና ኢያሱ ለእስራኤላውያን እግዚአብሔር የከነዓንን ሰዎች የማሸነፍ

ኃይል እንዳለው ነገሯቸው።

- እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር ለመግባት ተስማሙ?

ዘኁልቁ 14፡10ሀ

10- መላው ማኅበር ግን በድንጋይ ሊወግሯቸው ተነጋገሩ።

- እስራኤላውያን አሁንም ወደ ከነዓን ለመግባት አልፈለጉም።

- እስራኤላውያን አሁንም እግዚአብሔርን ለመታዘዝ አልፈለጉም።

- እስራኤላውያን ካሌብን ኢያሱንና ሙሴን በድንጋይ ሊወግሯቸው ፈለጉ።

- እስራኤላውያን ምን ይናገሩ እንደነበር እግዚአብሔር ሰምቶአል?
- አዎን።

- እስራኤላውያን ወደ ከነዓን ምድር መግባት እንዳልፈልጉ እግዚአብሔር አውቋል?

- አዎን።

- እስራኤላውያን አምላካቸው ከነዓናውያንን የማሸነፍ ኃይል እንዳለው አለማመናቸውን እግዚአብሔር አውቋል?

- አዎን።

- እግዚአብሔር ለእስራኤላውያን ከነዓንን ለመስጠት የገባውን ቃል

አለማመናቸውን አውቋል?

- አዎን።

- እስራኤላውያን እግዚአብሔር የከነዓንን ምድር ለእነርሱ ሊሰጥ የገባውን ቃል እንደሚጠብቅ አላመኑም።

- የእግዚአብሔርን ቃል ካላመንን እግዚአብሔርን ምን እያልነው ነው?
- ውሸታም።

- እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ቃል አላመኑም።
- እስራኤላውያን እግዚአብሔርን ውሸታም አሉት።

- እግዚአብሔር እንዲህ አላቸው፡

ዘኍልቁ 14፡26-32

26- እግዚአብሔር ሙሴንና አሮንን እንዲህ አላቸው፡

27- «ይህ ክፉ ማኅበረሰብ በእኔ ላይ የሚያጉረመርመው እስከ መቼ
ድረስ ነው? የእነዚህን ነጭናጮች እስራኤላውያን ማጉረምረም ሰምቻለሁ።

28- ስለዚህ እንዲህ በላቸው፤ ‘እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፤ እኔ
ሕያው ነኝ፤ ስትናገሩ የሰማኋችሁን እነዚያን ነገሮች አደርግባችኋለሁ፤

29- በተደረገው ቈጠራ መሠረት፣ ሃያ ዓመት ወይም ከዚያ በላይ
የሆናችሁና በእኔም ላይ ያጉረመረማችሁ ሁሉ በድናችሁ በዚህ ምድረ በዳ
ይወድቃል።

30- መኖሪያችሁ እንድትሆን በጽኑ ወደማልሁላችሁ ምድር ከዩፎኒ
ልጅ ከካሌብና ከነዌ ልጅ ከኢያሱ በስተቀር ከእናንተ አንዳችሁም
አትገቡባትም።

31- ይማረካሉ ያላችኋቸውን ልጆቻችሁን ግን አገባቸዋለሁ፤ እናንተ የናቃችኋትን ምድር እነርሱ ይደሰቱባታል።

32- እናንተ ግን፣ በድናችሁ በዚሁ ምድረ በዳ ወድቆ ይቀራል።’»

- እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ባለማመናቸው ምክንያት ወደ ከነዓን የገቡት እነማን ብቻ ነበሩ?

- ካሌብ ኢያሱና የእስራኤላውያን ልጆች ብቻ ነበሩ።

- እስራኤላውያን በእግዚአብሔር ባለማመናቸው ምክንያት እግዚአብሔር በምን ቀጣቸው?

- ወደ ከነዓን እንዳይገቡ በማድረግ።

- በምድረ በዳ እንዲሞቱ በማድረግ።

- እግዚአብሔር በእርሱ የማያምኑትን ሰዎች ሁልጊዜ በሞት ይቀጣል።

- የኖኅ ዘመን ሰዎች በእግዚአብሔር ስላላመኑ እግዚአብሔር በሞት ቀጣቸው።

- የሰዶምና ገሞራ ሰዎች በእግዚአብሔር ስላላመኑ እግዚአብሔር በሞት ቀጣቸው።

- ፈርዖንና ግብፃውያን በእግዚአብሔር ስላላመኑ እግዚአብሔር በሞት ቀጣቸው።

- እግዚአብሔር በእርሱ የማያምኑትን ሁሉ በዘላለማዊው የእሳት ባሕር ውስጥ በመጣል በሞት ይቀጣቸዋል።